# ምርጥ ምድጃ

## ከጭስ ማውጫ ጋር ተሻሽሎ የቀረበ!

- ለማገዶ የሚያወጡትን ወጪ በግማሽ ከመቀነሱም በላይ ብዙ ጭስ ስለሌለው በዓይንና በመተንፈሻ አካላት ላይ ከሚከሰተው የጤና ችግር ይድናሉ፡፡
- ዙርያው ዝግ ስለሆነ ከእሳት ወላፍንና ነበልባል ከመከላከሉም በላይ ለእሳት አደጋ አያጋልጥም፡፡
- ከባለ ሶስት ጉልቻ በተሸሻለ ፍጥነት ይጋግራል፡፡
- ማዕድ ቤታችን በንፅህና እንዲጠበቅ ይረዳናል፡፡
- በተሻሻለው ምርጥ ምድጃ ለባለ ሶስት ጉልቻ ምድጃ የምንጠቀምባቸውን የማገዶ አይነት (እንጨት፣ ኩበት፣ የሰብል ቃርሚያ ወዘተ .....) መጠቀም ይቻላል ፡፡
- ዋጋውም ከህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ጋራ ተመጣጣኝ በመሆኑ ብዙዎች ገዝተው ይጠቀሙበታል፡፡

ስለሆነም በተሻሻለው ምርጥ የእንጀራ ምድጃ በመጠቀም ገንዘብዎን ይቆጥባሉ፣ ጤናዎትን ይጠብቃሉ፣ በተጨማሪም የደን ሀብታችንን በመንከባከብ የበኩልዎን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

## 150,000 ምርጥ ምድጃዎች በአገለግሎት ስራ ላይ ቢውሉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይገኛሉ፡-

- የሚቆጠበው የእንጨት መጠን በየዓመቱ 86,250 ቶን ይሆናል፡፡
- በአጠቃላይ ወደ 31,500,000 ብር ለማገዶ ወጪ ከመሆን ይድናል (ይህም ለሌላ ጥቅም ይውላል)፡፡
- በየዓመቱ 11,250 እስከ 15,000 ሄክታር የሚሆን ደን ከመጨፍጨፍ ይድናል (ባህር ዛፍ)፡፡
- ይህ ደን ቢጨፈጨፍ ኖሮ እርሱን ለመተካት ለዛፍ ተከላ ያስፈልግ የነበረ ወደ 71,250,000 ብር አሁን ለሌላ ጥቅም ሊውል ይችላል፡፡
- በአጠቃላይ የሚፈጠረው ጭስ ስለሚቀንስ የአከባቢ አየር መበከልን ይቀንሳል፡፡ የተረፈውም ደን የተፈጥሮ ሚዛንን ለመጠበቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ምርጧ

ሲጋግሩ በጭስ መመረዝ ቀረ!

ከጭስ ማውጫ ጋር ተሻሽሎ የቀረበ!